# ወደ ፊልሞና

፩ የክርስቶስ ኢየሱስ እስር ጳውሎስ ወንድሙም ጢሞቴዎስ፥
ለተወደደውና አብሮን ለሚሠራ ለፊልሞና፥ ፪ ለእኅታችንም
ለአፍብያ፥ ከእኛም ጋር አብሮ ወታደር ለሆነ ለአርክጳ፥
በቤትህም ላለች ቤተ ክርስቲያን፤ ፫ ከእግዚአብሔር ከአባታችን
ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።
፬-፮ የእምነትህም ኅብረት፥ በእኛ ዘንድ ያለውን በጎ ነገር ሁሉ
በማወቅ፥ ለክርስቶስ ኢየሱስ ፍሬ እንዲያፈራ እለምናለሁ፤
፯ የቅዱሳን ልብ በአንተ ስራ ስለ ዐረፈ፥ ወንድሜ ሆይ፥ በፍቅርህ
ብዙ ደስታንና መጽናናትን አግኝቼአለሁና። ፰ ስለዚህ የሚገባውን
አዝህ ዘንድ በክርስቶስ ምንም እንኳ ብዙ ድፍረት ቢኖረኝ፥
፱ ይልቁንም እንደዚህ የሆንሁ እኔ ጳውሎስ ሽማግሌው፥ አሁንም
ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ እስር የሆንሁ፥ ስለ ፍቅር እለምናለሁ።
፲-፲፪ እርሱን እልከዋለሁ፤ ፲፫ አንተም ልቤ እንደሚሆን
ተቀበለው። እኔስ በወንጌል እስራት ስለ አንተ እንዲያገለግለኝ
ለራሴ ላስቀረው እፈቅድ ነበር፥ ፲፬ ነገር ግን በጎነትህ በፈቃድህ
እንጂ በግድ እንዳይሆን፥ ሳልማከርህ ምንም እንኳ ላደርግ
አልወደድሁም። ፲፭ ተቀብለህ ለዘላለም እንድትይዘው ስለዚህ
ምናልባት ለጊዜው ተለይቶሃልና፤ ፲፮ ከእንግዲህ ወዲህ እንደ
ባሪያ አይሆንም፥ ነገር ግን ለእኔ በተለየ የተወደደ ወንድም
ከሆነ፥ ለአንተማ ይልቅ በስጋውም በጌታም ዘንድ ከባሪያ
የሚሻል የተወደደ ወንድም እንዴት አይሆንም። ፲፯ እንግዲህ
እንደ ባልንጀራ ብትቈጥረኝ፥ እንደ እኔ አድርገህ ተቀበለው።
፲፰ በአንዳች ነገር የበደለህ ቢኖር ግን ወይም ብድር ያለበት
እንደሆነ፥ ይህን በእኔ ላይ ቍጠር፤ ፲፱ እኔ ጳውሎስ። እኔ
እመልሰዋለሁ ብዬ በእጄ እጽፋለሁ፤ ከዚህም በላይ ለእኔ
የራስህ ደግሞ ብድር እንዳለብህ አልልህም። ፳ አዎን፥ ወንድሜ
ሆይ፥ በጌታ እኔ እንድጠቀምብህ ይሁን፤ በክርስቶስ ልቤን
አሳርፍልኝ። ፳፩ ከምልህ ይልቅ አብልጠህ እንድታደርግ አውቄ
እንድትታዘዝም ታምኜ እጽፍልሃለሁ። ፳፪ ደግሞ ከዚህም
ጋር የማስተናገጃ ቤት አዘጋጅልኝ፤ በጸሎታችሁ ለእናንተ
እንድሰጥ ተስፋ አደርጋለሁና። ፳፫ በክርስቶስ ኢየሱስ ከእኔ ጋር
የታሰረ ኤጳፍራ ፳፬ አብረውኛም የሚሰሩ ማርቆስና አርስጥሮኮስ

ዴማስም ሉቃስም ሰላምታ ያቀርቡልሃል። ፳፭ የጌታችን የኢሱስ
ክርሰቶሰ ጸጋ ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን።

# መጽሐፍ ቅዱስ
# The New Testament in the Amharic language of Ethiopia

copyright © 1962, 2003 United Bible Societies

Language: አማርኛ (Amharic)

**Amharic NT**

Revised Amharic Bible in XML (2003).

Printed version by United Bible Societies (C)1962.

E-Text in transliterated ASCII format by Lapsley/Brooks Foundation 1994.

Unicode UTF-8 transformation and XML-tagging by Dirk Röckmann 2003 (www.nt-text.net).

With kind permission of the Bible Society of Ethiopia.

Every non-commercial work using this data in any form must fully include this copyright statement!

Every commercial use of parts or the complete data in any form needs written permission of the Bible Society of Ethiopia!

2014-09-09

---

PDF generated using Haiola and XeLaTeX on 11 Nov 2022 from source files dated 9 Oct 2020
2432e07d-4260-5d76-afcb-ce35bd1c48b7